

# የሳኪማ መዝሙር

Ursula Nafula
Peris Wachuka
Dawit Girma
Amharic
Level 3



ሳኪማ ከቤተሰቦቹና ከ4 ዓመት ታላቅ እህቱ ጋር ይኖራል። የሚኖሩት ባንድ ሃብታም ሰውዬ መሬት ላይ ነው። ባለሳር ክዳን ጎጇቸው በመደዳ ከበቀሉ ዛፎች ማዶ ትገኛለች።



ሳኪማ 3 ዓመት ሲሆነው ታመመና የዓይን ብርሃኑን አጣ። ሳኪማ ባለተሰጥኦ ልጅ ነበር።



ሳኪማ የ6 ዓመት ልጆች እንኳ የማይሰሯቸውን በርካታ ነገሮችን ማድረግ ይችላል። ለምሳሌ ከመንደሩ ትልልቅ ሴቶች ጋ ቁጭ ብሎ ጠቃሚ ቁምነገሮችን ይወያያል።



የሳኪማ ቤተሰቦች በሃብታሙ ሰው ቤት ውስጥ ይሰራሉ። ጠዋት በማለዳ ከቤታቸው ይወጡና ማታ ወደቤታቸው ይመለሳሉ። ሳኪማ ደግሞ ከትንሽ እህቱ ጋር ይቆያል።



ሳኪማ መዝሙር መዘመር ይወዳል። አንድ ቀን እናቱ ጠየቀችው፣ ‹‹ከየት ነው እነዚህን መዝሙሮች የተማርካቸው ሳኪማ?››



ሳኪማም መለሰ ‹‹ራሳቸው ይመጣሉ እማዬ። በጭንቅላቴ እሰማቸዋለሁ ከዚያም እዘምራለሁ።››



ሳኪማ ለእህቱ ይዘምርላታል በተለይ ሲርባት ሲርባት። ተወዳጅ ዜማዎቹን ሲያዜም እህቱ ትሰማዋለች። ወዲያ ወዲህ እየተወዛወዘች በዜማው ትመሰጣለች።



‹‹ደግመህ ደጋግመህ ልታዜምልኝ ትችላለህ ሳኪማ›› እህቱ ለመነችው። ሳኪማም ጥያቄዋን ተቀብሎ እስኪበቃት ደጋግሞ አዜመላት።



አንድ ምሽት ቤተሰቦቹ ወደቤት ሲመለሱ በጣም ተክዘው ነበር። ሳኪማ የሆነ ነገር እንደተፈጠረ አወቀ።



‹‹እማዬ፣ አባዬ ምንድነው? ምን ችግር አለ?››
ሳኪማ ጠየቀ። የሃብታሙ ሰው ልጅ መጥፋቱን
ሳኪማ ተረዳ። ሰውዬው በጣም አዘነ፣ ብቸኝነትም
ተሰማው።



‹‹አዜምለታለሁ። እንደገናም ደስተኛ ይሆናል›› አለ ሳኪማ ለቤተሰቦቹ። ቤተሰቦቹ ግን ጆሮ ዳባ ልበስ አሉት። ‹‹እሱ በጣም ሃብታም ነው። አንተ ደግሞ ተራ አይነ ስውር ነህ። የአንተ ዜማ የሚረዳው ይመስልሃል?››



ነገር ግን፣ሳኪማ ተስፋ አልቆረጠም። ትንሿ እህቱም ትረዳዋለች። ‹‹የሳኪማ ዜማዎች በራበኝ ጊዜ ያረጋጉኛል። ሃብታሙን ሰውዬም እንዲሁ ያረጋጉታል።››



በቀጣዩ ቀን ወደ ሃብታሙ ቤት መርታ እንድትወስደው ሳኪማ እህቱን ጠየቃት።



ከአንድ ትልቅ መስኮት በታች ቆሞ ተወዳጁን ዜማ አዜመ። ቀስ ብሎ የሃብታሙ ሰው ጭንቅላት በትልቁ መስኮት በኩል መታየት ጀመረ።



ሰራተኞቹ እየሰሩ የነበረውን አቆሙ። የሳኪማን ቆንጆዬ ዜማ ማዳመጥ ጀመሩ። ነገር ግን አንድ ሰው እንዲህ አለ ‹‹ማንም ሰው ቢሆን አለቃችንን ሊያዝናናው ወይም ሊያጽናናው የሚችል የለም። ይሄ አይነ ስውር ልጅ የሚችል ይመስለዋል እንዴ?››



ሳኪማ ማዜሙን ጨረሰና ሊመለስ ሲል ሃብታሙ ሰውዬ ፈጥኖ ወጣና <<እባክህ እንደገና አዚም>> አለው።



በዚያው ቅጽበት ሁለት ሰዎች በቃሬዛ አንድ ሰው ይዘው መጡ። የሃብታሙን ሰውዬ ልጅ ተነክሶ ጉዳት ደርሶበት መንገድ ዳር ወድቆ ነው ያገኙት።




ልጁን ደግሞ ስላየው ሃብታሙ ሰውዬ በጣም ተደሰተ። ምቾት ስለሰጠው ሳኪማ ተደሰተ። ከዚያ ልጁንና ሳኪማን ወደ ሃኪም ቤት ወሰዳቸው፤ሳኪማም እንደገና አይኑ ማዬት ቻለ።

# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## የሳኪማ መዝሙር

Written by: Ursula Nafula
Illustrated by: Peris Wachuka
Translated by: Dawit Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 4.0 International License.